# ኢትዮጵያ ብትመች

*(ፍቅሬ ቶሎሳ፥ ፒ ኤች ዲ*

*(የሁማኒቲስ ፕሮፌሰር)*

አንተ የደላህ ሰው ሁሉን ለራስ ይዘህ፥ ተው ግፍ
አትናገር፥ "ወጣቱን ከሃገር ማን ውጣ አለው?" ብለህ፥
ሕሊናህ ደንዞ በምቾትህ ብዛት፥ የወጣቱን ስቃይ
ተስኖህ መረዳት፤ኧረ ተው አትቅጠፍ አውነቱን አብለህ!!!

ወጣቱ ለአንግልት፥ ቁምስቅል ለማየት
ለ 'ስርና ለሞት፥ ለጠኔና እርዛት እራሱን አጋልጦ፥ መች
በተሰደደ ባህር ላይ ለመትነን፥ በርሃ ለመብነን፥ደሞ
ለመዘረፍ ኩላሊት ጉበቱን፤ ሊታረድ አንገቱን፥ አገሯ ብትመች?

ተምሮ ለመሥራት፥ ሠርቶ ለመንበሽበሽ፥
መንበሽበሹም ቢቀር፥ለመብላት፥ ለመልበስ፥መች
ይሰደድ ነበር ተነቅሎ ካገሩ፥ ርቆ ከወላጁ፤
ሠርቼ ልኑር ሲል ኢትዮጵያ ብትመች?

ማን ቢያምር ይጠላል ተከብሮ ባገሩ፥
የመናገር፥መፃፍ ቢረጋገጥ መብቱ፥ መች
በኮበለለ ቢዳኝ በትክክል፥
ፍትህ ርት ለማግኘት ኢትዮጵያ ብትመች?

ፎቁ ተከምሮ፥ አስፋልቱ ተነጥፎ፥
በረንዳ ባያድር ወይም ከጉረኖ፥ ቢፎልል ባስፋልቱ፥መች
ሞት በመረጠ፥ ከልማት ከሀብቱ ቢያገኝ ፍርፋሪ፥
ሸቅሎ ለማደር አገሯ ብትመች?

የተማረች ሴት ልጅ ስትፈልግ ሥራ፥ልተኛሽ ባይላት፥
አያ እናት-አይምሬው፥ ወራዳው ቀጣሪ፥መች
ትነጉድ ነበር፥ ካውሬ ለሚከፋው ልትሆን ያረብ ገረድ፥
ክብሯ ባይደፈር፥ ኢትዮጵያ ብትመች?

ሀሁ ያላለፈ፥ ዲፕሎማ ሸማቹ እፍረተ-ቢስ ሁላ፥
የማይገባውን ወፍራም ደሞዝና፥ ማዕረግ ባይሸከም፥መች
ሥራ በአጣ የተማረው ለፍቶ፤
መች ከፍቶት በሄደ አገሯ ብትመች?

ጉዳዩ ሳይታይ፥ በተፈጠረ ክስ እስርቤት ባይማቅቅ፥
በዱላ ውርጅብኝ ናላው ባይቃወስ፥ አከላቱ ባይጎል፥ መች
በሸሸ ነበር፥ ሰውነቱ ታውቆ ሰብዕናው ቢከበር፥
አምባመግነን ባይኖር፥ ለህግ በላይነት ኢትዮጵያ ብትመች?

በምርጫ ውድድር የአሻውን ቢመርጥ፥ ምርጫው ቢሆን የሃቅ፥
ሲያሸንፍ ቢያሸንፍ፥ቢኖር ዲሞክራሲ፥መች
ይፈልስ ነበር አገር ሙሉ ወጣት፥
አውነት ለያዘ ሰው አገሯ ብትመች?

እራስዋን ሰብስባ፤ ላመታት ተምራ የሴት ልጅ ዕጣዋ፥
ባይሆን የወንድ በታች፤ ባይሆን ከቡና ቤት፤ መች
ምርር ብላ ገብታ ካረብ አገር፥
ህይወቷን ባጣችው ኢትዮጵያ ብትመች?

ወንድ ልጅ አንብቶ፥ ከህዘኑ ብዛት
ካይኑ መግል ፈስሶ፥ ተስፋው ተደምሶ፥ መች
በ'ርሮ በጠፋ፥ በግብረሰዶሞች ባረብ ፍናፍንቶች፥
ተደፍሮ በርኩሠት ወንድነቱን ሊያጣ፥አገሯ ብትመች?

በዘር፥ ጎሳ ሳይሆን፥ በትውውቅና ወይም በዝምድና፥
ሠርቶ መኖር ቢችል በችሎታው ብቻ፥ መች
አገር በተወ፥ የባሰስ አይመጣም ብሞት ልሙት ብሎ
ለሃቅ አስተዳደር ኢትዮጵያ ብታመች?

አንድ "ምርጥ" ወገን ባገር ተንሰራፍቶ፥
የበዪ ተመልካች ሌላው ባይሆን ኖሮ፥ መች
በተሰደደ ወጣቱ ከቀዬው
ለዜጋዎች ሁሉ አገሯ ብትመች?

ኢትዮጵያችን ሆና ለህዝቧ ሁሉ እኩል፥
ቢሰማው ወጣቱ የኩልነት ስሜት፥መች
ይነጉድ ነበር ነፃነት አሰሳ፥
ለእኩልነት ኑሮ ምድሯ ብትመች?

ኢንጂነር፥ መሃንዲስ ለፍቶ ጥበብ ቀስሞ፥
ድንጋይ ማንጠፍ ባይሆን የሱ ዕጣ ፈንታ፥ መች
በሸመጠጠ ተገቢው ተከፍሎት፤
ሙያው እንዳይባክን አትዮጵያ ብትመች?

ያረጀ መጦሪያ በሌለበት አገር፤
አናት አባት መጦር አቅቶት ወጣቱ፥መች
ይመርሽ ነበር ተጧሪ እሱ ባይሆን፤
ኅሊናው ባይደማ አገሯ ብትመች?

ኪስ ያልገባው ደሞዝ ሳይገባ ባይወጣ፥
ከ እጅ ወዳፍ ባይሆን የመናወዝ ዋጋው፥መች
ይዘምት ነበር ወጣት ግርርር! ብሎ፥
የድካም ለማግኘት ኢትዮጵያ ብትመች?

ልጅ ቀማኛ ሲሆን አባት ባይሆን ዳኛ፥
ባይገመደል ፍርድ ባይኖር ኖሮ አድልኦ፥መች
እግሬ አውጭኝ ባለ ተስፋ አጥቶ ወጣቱ፥
ለፍትህ መሟላት አገሯ ብትመች?

አንድ ልብስ ለመግዛት፥ ዕቃ ለመሸመት
በቀን አንዴ በልቶ ባይባዝን አንድ ዓመት፥መች
ይባክን ነበር ወጣቱ ዱር ለዱር፥
መች ባሕር ይሰምጣል ኢትዮጵያ ብትመች?

ወጣቱ ባገሩ ጥላና ከለላ፥ ቢኖረው መከታ፥
ቢኖረው ውርስ ቅርስ፥ ንብረትና መሬት፤ መች
ይተምም ነበር በሰይፍ ሊቀላ፥በአሳት ሊቃጠል፥
በገመድ ሊታነቅ፥ አገሯ ብትመች?

ሳያሽቃብጡና ሳያጎበድዱ፥ አየነፉ ደረት
ደንብ ተከትለው ሀይወትን ቢኖሩ፥ መች
በሸመጠጠ፥ ለመፈፀም ቢችል ፍጹም ንጹህ ተግባር፥
በራስ ለሚኮራ፥ ሙስናን ለጠላ ኢትዮጵያ ብትመች?

ደሞም ገዥው ባይለው አኔን ካልደገፍከኝ
አልሰጥህም ሥራ ቢሻህ በጠኔ ሙት፥ መች
አገሩን ረግሞ ሆድ ብሶት በጠፋ፥
አልወግንም ላለ አገሯ ብትመች?

በሀቅ ነግዶ ባግባቡ ቢቀረጥ፥ ንግዱ ችርቻሮው
ለሁሉ ቢዳረስ፥ ባይያዝ በጥቂት፥ መች
በፈረጠጠ ወጣት ድንበር ጥሶ፥
አትርፎ ለመኖር አትዮጵያ ብትመች?

ወይም አርሶ እንዳይኖር መሬቱን ተነጥቆ፥መርዛም ማዳበሪያ
ሸምቶ በግዳጅ ባይያዝ በዕዳ፤ ከዕትብቱ መሬት ባይነቀል ኖሮ፥መች
ዘሎ በሄደ ውቅያኖስ ማዶ፥ በነፍሱ ላይ ፈርዶ፥
አፈር ለሚገፋ፥ ለከተሜው-አብዩ አገሯ ብትመች?

አንተ የደላህ ሰው ሁሉን ለራስ ይዘህ፥ ተው ግፍ
አትናገር፥ "ወጣቱን ከሃገር ማን ውጣ አለው?" ብለህ፥
ሕሊናህ ደንዞ በምቾትህ ብዛት፥ የወጣቱን ስቃይ
ተስኖህ መረዳት፤ኧረ ተው አትቅጠፍ አውነቱን አብለህ!!!

አሁን ትናትና፥ ከርታታ አንደነበርክ
ምስኪንና ጭቁን፥ ከመቼው ተረሳህ
በምቾት ደንድነህ፥ ዛሬ ለከርታታው
ግንዛቤ ጎድሎህ ርሕራሔ የነሳህ?

አወይ ሥልጣን እኩይ! አወይ ምቾት ክፉ፥
ካይን ጥቅሻ ፍጥነት ድህነት ያስረሳል፥
ሕሊና አደንድኖ ልብን ይሰውራል፥
በትዕቢት ወጥሮ ለጥፋት ያደርሳል።

በሰራዊት ብዛት ጦር እንደማያሸንፍ
ካሳለፍከው ሕይወት አንደምን አታውቅም፥
አንዴት ተዘነጋህ ጊዜ እንጂ የሰው ልጅ
ለሱ ቢመስለውም አንደሌለው አቅም።

አናም በጦር ብርታት ተው አትቀናጣ፥
በጦር የተመኩ በንነዋል አንደጢስ፥
ውድቀት፥ ውርደት ስበው፥
ብረት አንደሚስብ፥ አንደ መቀነጢስ።

ከቶ የማይማር ከአለፈው ታሪክ

የትናንትናውን ማንነት ዘንግቶ፥

እንደሌሎች ሁሉ ደንድኖ ሲዝናና

ባፍ ጢሙ ይደፋል በጊዜ ተረቶ፥ በዘመን ታግቶ።

ጊዜ ያነሳውን እሽቅብ ተኩሶ፥

ግፍ አዳላጭ ሆኖ ቁልቁል ሲከሰክስ፥

ፍርድ ይስተካከላል፤ ፍትህ ይበቀላል፥

የድሃ እምባን ሊያብስ፥ ተበዳይን ሊክስ ።

አኤአ ግንቦት 2 ቀን 2015

ሻሌሆ፥ ካሊፎርኒያ

**ፕሮፌሴር ፍቅሬ ቶሎሳ፥ በ** lulu.com **እና** Amazon.com **ላይ በገበያ የዋለው፥ የ** *Hidden and Untold History of The Jewish People and Ethiopians* **ደራሲ ነው።** *Heaven To Eden* **የተሰኘው ተራኪ፥ ፍልስፍናዊና ግጥማዊ ተውኔቱ በቅርቡ ለ ዐዓለም አንባብያን ይቀርባል። አስተያየት በ** fiktolo@gmail.com **ይቀበላል።።**